የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-lion@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. ____________
ቀን
Date ____________

**ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

የ2002 ዓ.ም ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ግንቦት 15/2002 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ምርጫ ሕግና፣ ከመራጩም ሕዝብ ፈቃደኝነት ውጭ መፈፀሙን ከመላው ኢትዮጵያ ክልሎች ከየአቅጣጫው ከሚደርሱን ሪፖርቶች ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በሁሉም የምርጫ ክልሎች

1. በሕግ የተወሰነውና ከምርጫ ቦርድም በተሰጠው መመሪያ መሠረት ታዛቢዎቻችን ከሌሊቱ 11 ሰዓት በየምርጫ ክልሉና በየምርጫ ጣቢያዎቹ ከመገኘታቸው በፊት የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት በመጀመራቸው ቁጥጥር ባልተደረገበት ሁኔታና ኮሮጆው ሳይፈተሽ የድምጽ መስጫ ካርዶች ሳይቆጠሩ ምርጫው በመጀመሩ፤
2. የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና የቀበሌ አመራሮች በቡድን በቡድን በመሆን የምርጫ ጣቢያዎች አጠገብ ቁልፍ ቦታዎች በመያዝ ኢሕአዴግን ነው የምትመርጡት በማለት መራጩን ሕዝብ በማስፈራራታቸው፣
3. በየምርጫ ጣቢያው የታደሉት የምርጫ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች በመራጭነት ከተመዘገበው ሕዝብ በላይ በገፍ የተሰራጩ ከመሆናቸውም በላይ በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ለምርጫ ከተመዘገበውና ከመረጠው ሕዝብ ቁጥር በላይ የሆነ ድምጽ የተሰጠበት ወረቀት በምርጫ ሳጥኖች ውስጥ መገኘታቸው፡፡
4. የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በየአንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ለምርጫ የሚቀርበውን ሰው ስሙን እየመዘገቡና በስሙ አቅጣጫ ምልክት እያደረጉ በመራጩ ሕዝብ ላይ የሥነ-ልቦና ተጽኖ ከማድረጋቸውም በላይ ከላይ በተጠቀሰው የመቆጣጠሪያ ዘዴያቸው መሠረት ያልመጣውን ሰው ከየቤቱ በስልክ የሚጠሩ ሲሆን በዚህ ሁኔታ በተጽዕኖ

ሥር ወድቆ ለምርጫ የመጣውን ሰው ማንን እንደሚመርጥ በግልጽ ትእዛዝና መመሪያ ሲሰጡ በመዋላቸው፣

5. ለመራጩ ሕዝብ የአመራረጥ ገለጻ የሚያደርጉት የየምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈጻሚዎች በገለጻቸው ላይ የኢህአዴግን ምልክት ብቻ በማሳየት በመራጩ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ ማሳደራቸው፣

6 በየምርጫ ጣቢያው የተገኙት የፓርቲያችን ታዛቢዎች ያዩት ስህተት እንዲመዘገብላቸውና በወቅቱም እንዲታረም ሲጠይቁ ፖሊስ እየተጠራ ተገደው እንዲፈርሙ መደረጉ፣

በተለይ ታዛቢዎች ተደብድበው እንዲባረሩ ወይም እንዲታሰሩ በማድረግ ምርጫ የተካሄደባቸው የምርጫ ክልሎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

I. <u>ትግራይ</u>

1.1. ደቡብ ትግራይ ዞን ባሉት የምርጫ ክልሎች በሙሉ

II. <u>አማራ</u>

2.1. ሰሜን ጎንደር ከጎንደር ከተማ ውስጥ በቁጥር 1,2 እና 3 በከፊል የተባረሩ ሲሆን በጎንደር ቁ.4 እና ገጠር ያሉት በሙሉ ተባርረዋል፡፡

2.2. ደቡብ ጎንደር በሙሉ፤

2.3. ሰሜን ወሎ በሙሉ፤

2.4. ደቡብ ወሎ በሙሉ፤

2.5. ምዕራብ ጎጃም ከባሕር ዳር ከተማ በስተቀር፤

2.6. ምሥራቅ ጎጃም ከደብረማርቆስ ከተማ በስተቀር፤

2.7. አዊ ዞን ከምርጫው በፊት አንድ ቀን ሲቀረው ታዛቢዎች ተደብድበው ታስረው ካደሩ በኋላ በምርጫ ቀን በታዛቢነት እንዳይሳተፉ ተደርገዋል፡፡

2.8. ሰሜን ሸዋ በሙሉ፤

III. <u>ኦሮሚያ</u>

3.1. ምሥራቅ ሸዋ በዝዋይና መቂ የምርጫ ክልሎች፤

3.2. ምዕራብ ሸዋ በሙሉ

3.3. ደቡብ ምዕራብ ሸዋ

ዓለምገና በሁለቱም የምርጫ ክልሎች

3.4. አርሲ

በሶስት የምርጫ ክልሎች

3.5. ቦረና በሙሉ

3.6. ጉጂ በሙሉ

## IV <u>አፋር</u>

በሶስት የምርጫ ክልሎች

## V. <u>ደቡብ ብሔር/ብሔረሰቦች</u>

5.1. ወላይታ ዞን በሙሉ ከሶዶ ከተማ በስተቀር

5.2. ሀዲያ

- በሰቂ የምርጫ ክልል

5.3. ከንባታ በሶስት የምርጫ ክልሎች

5.4. ጉፋ እና አይዳ ልዩ ወረዳ ጨምሮ በሙሉ

5.5. ጋሞ በሙሉ

5.6. ጌዲዮ በሙሉ

5.7. ሐዋሳ ካሉት ሶስት የምርጫ ክልሎች በሁለቱ በሙሉ ተባርረዋል።

5.8. ሲዳማ በሁሉም የምርጫ ክልሎች

በደቡብ ከድምጽ መስጫው እለት በፊት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በቅድሚያ ለኢህአዴግ ተሞልተው በመገኘታቸው ለአውሮፓ ዩኒየን ታዛቢዎች አቅርበናል።

## VI. <u>አዲስ አበባ</u>

6.1. በምርጫ ጣቢያዎች አካባቢ በቅርብ ርቀት በመሆን በቡድን ተደራጅተው መራጩ ሕዝብ ኢህአዴግን እንዲመርጥ ከመቀስቀስ በተጨማሪ ያስፈራሩ ነበር።

6.2. ቀደም ሲል ያልተመደበ አዲስ ድምፅ መስጫ ጣቢያ በመክፈት ካለታዛቢዎች ምርጫ እንዲከናወን ተደርጓል። ለምሳሌ ወረዳ 23፣ ወረዳ 4 ወዘተ…

6.3. የምርጫ ድምፅ መስጫ ወረቀት ኢህአዴግ የተመረጠበት የጣት አሻራ ያለበት በሚስጢር ድምፅ መስጫ ክፍል ተገኝቶ የምርጫ አስፈጻሚዎች ይቅርታ በማለት ጠይቀዋል። ለምሳሌ ወረዳ 12/13፣

6.4. ዓይነ ሥውራንና ሽማግሌዎች ሲመጡ የምርጫ አስፈጻሚዎች ይመርጡላቸው እንደነበር ተረጋግጣል፡፡ ለምሳሌ ወረዳ 12/13፣ ወረዳ 1/9

6.5. የመኢአድ ምልክት አቅጣጫው ከመቀየሩም በላይ ከሌሎች እጅግ አነስተኛ ሆኖ በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

6.6. የመኢአድ የምርጫ ታዛቢ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 21/22፣ የምርጫ ጣቢያ 15/16 ተባሯል፡፡

6.7. ሦስት መራጮች በመዝገብ ተመዝግበው እያሉ እንዳይመርጡ ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ በጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 10 ጣቢያ 07-17፣ ወዘተ…

6.8. ታሪኩ በቀለ የሚባል በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 16 የምርጫ ክልል 03 ሁለት የምርጫ ካርድ ይዞ በመገኘቱ እንዳይመርጥ ተደርጓል፡፡

6.9. በብዙ ወረዳዎች የምርጫ ክፍሉ ሚስጥራዊ አልነበርም፡፡ በተለይም ክፍሎቹ የተያያዙ እና መራጮች ለመተያየት እና ለመነጋገር የሚያስችል ሁኔታ እንደነበረ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ ወረዳ 12/13 የምርጫ ጣቢያ 01-1፣ ወረዳ 1/9፣ ወረዳ 19፣ ወዘተ…

6.10. የኢህአዴግ ካዲሬዎች በየምርጫ ጣቢያ አካባቢ ተሰማርተው ኢህአዴግን አንመርጥም ያሏቸውን እንግዲያውስ ✓ ምልክት ያድርጉበት እያሉ የምርጫ ድምፁ እንዲበላሽ ይቀሰቅሱ ነበር፡፡

ባለፉት ሶስት ወራት የነበረው የምርጫ ሂደት ነጻ፣ ፍትሐዊና ተአማኒ እንዳልነበረ በተለያዩ ደብዳቤዎች መግለጻችን እና ችግሮቹ እንዲታረሙ መጠየቃችን ይታወሳል፡፡ በምርጫው እለትና ከምርጫው በኋላ ከምርጫው ጋር በተያያዘ በርካታ ዜጎች ተደብድበዋል፣ ከመኖሪያቸው ተባረዋል፣ ታስረዋል፣ ሰብአዊ መብታቸው ተገፎ የተለያዩ እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ በመሆኑም የምርጫው ሂደት እና ውጤት ተአማኒነትና ፍትሐዊነት የሌለው፣ በመራጩ ሕዝብ ፍላጐት ያልተከናወነ፣ ገዢው ፓርቲ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲል ከምርጫ አዋጁ ውጭ በራሱ የደህንነትና የፓርቲ አባላት ከፍተኛ አፈና ሥር ሆኖ ያካሄደው መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

ምርጫው በፓርቲዎች ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ ሀ እና ለ መሠረት የተፈፀመ ባለመሆኑ በፓርቲዎች ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 662 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ይህንን አቤቱታ ለቦርዱ አቅርበናል፡፡

በአጠቃላይ ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ ያለመሆኑን ገልፀን በየምርጫ ክልሉ አቤቱታችንን ለማቅረብ ሞክረን ከምርጫው ፍጻሜ ሰዓት ጀምሮ የየክልሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች በቦታቸው ባለመገኘታቸውና አቤቱታችንም አገር አቀፍ ያሉትን ሁሉንም የምርጫ ክልሎች የሚያጠቃልል በመሆኑ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ቁጥር 532/1999 አንቀጽ 96/3/ መሠረት ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅርበናል፡፡

በመሆኑም የምርጫውን ውጤት ለመቀበል የሚያስችል ተአማኒነት ያለው ሁኔታ ባለመኖሩ፣ ይልቁንም እንዲህ ያለው የአንድ ፓርቲ መቶ በመቶ ድምጽ ማግኘት ሂደቱ እና ውጤቱ ከላይ ባሳየነው መሠረት አጠያያቂ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምርጫው የሕዝብን የድምጽ መስጠት መብት በማፈን በአገሪቱ የዲሞክራሲያዊ ሂደት ላይ የማይፈለግ ጥቁር ጥላ ያጠላበት ሁኔታ ስለተፈጠረ ጠቅላላ ምርጫውን ለመቀበል አይቻልም፡፡ በመሆኑም ነጻና ፍትሐዊ፣ በሕዝብ ተቀባይነት ያለው ምርጫ እንደገና እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር